# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 7 ልዩ ዕትም 1 ታህሳስ ፲፱ ቀን ፪ ሺህ ፲፪ ዓ.ም.

## ዝክረ ጥላሁን ግዛው፦ 50ኛ ዓመት

*(ታህሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም. ጥላሁን ግዛው የተሰዋበትን 50ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)*

*ግጥሙን በድምሽ ቅጂ ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ* (*https://www.youtube.com/watch?v=fnwYVCHFceA&t=0*)

**ጥላሁን፦** ሩቅ አሳቢ፤ ቅርብ አዳሪ
ታሪክህ ህያው፤ ኮከብ አብሪ
መሬት ለአራሹ ጩኸትህ
ዛሬም ትግል ላይ ነው መፈክርህ።

**ጥላሁን፦** የሀብታም ልጅ፤ ለድሃ ሟች
የንጉሥ ዘር፤ ፍቅርህ ለሀገር
መፈክርህ፤ ድሃ ይማር!
የህዝባችን መብት ይከበር!
መሬት ለአርሶ አደር!
ኢትዮጵያችን ሁሌም ትኑር!

**ጥላሁን፦** የድሃ ማግኘት ያንተ ደስታ
በነበር ተወስተው፡ ቆሻሻና በሽታ
ሕጻናት ቦርቀው፡ ተላቀው ካንቀልባ
ሀገር ለሕዝብ ሁና፡ ኢትዮጵያችን አብባ
ስልጣኔ ሰፍቶ፡ ሀገርህ ከፍ ብላ
ነበረ ምኞትህ፡ በጥይት ተበላ።

**ጥላሁን፦** በሺህ ዘጠኝ መቶ 62፣
ሠፈረ አፍንጮ በር
በታህሳስ ገብርኤል፤
ስትጠልቅ ጀምበር
ያ ሩቅ አሳቢ፡ ሆነ ቅርብ አዳሪ
በግፈኞች በትር፡ በጥይት በራሪ
የትግል ምሰሶ፡ ጥላሁን ግዛው
ሆነ ተቀባሪ፡ ገና ሳይጀምረው፡ ።

**ጥላሁን፦** የታጋይ እረፍቱ ሞቱ
እንኳን አረፍክ፡ ከጩኸቱ
ኖረህ፡ ዘር ከመቁጠር
ከመሰደድ፡ ርቀህ ከሀገር
ኖርኩኝ ከማለት፡ ርቀህ ከሕዝብ
ታገልኩ ከማለት፡ ባዶ ሆነህ
እንኳን ተኛህ፡ ታሪክ ሰርተህ።

**ጥላሁን፦** የጮህክለት አርሶ አደር
ብለህ፡ መሬት ይገባዋል
መጤ ተባለና፡ ሲገባ ከገደል
ሜንጫና ገጀራ፡ በወገን ላይ ሲውል
ሀገር ወራሪ አጥታ፡ እኛው ስንሆን ጠላት
ሰንደቅ ዓላማዋ፡ ጨርቅ ሁኖ ልንከፋፍላት
እንኳንስ አሸለብክ፡ ይህን ከማየት፣
ከዚህ ሁሉ መሀት?



ጥላሁን ግዛው
Tilahun Gizaw

**ጥላሁን፦** ኮለል ሲል የታጋይ ደም
በአርኣያህ ታሪክ ሲደግም
በፈለግህ ጥይት ሲቃም
ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ?” የዘመረ
በአደባባይ ተዘረ. . .ረ . . .
ትግል ሞተ፤ ተ.ቀ.በ.ረ.
ገዳይ ነግሶ ተከበረ።

**ጥላሁን፦** ትግልን የከዳ፤ አሽቃባጭ ባንዳ
ግራ፣ ቀኝ መንገደኛ፤ ከሀዲ አንጀኛ
አድርባይ ምሁር፤ ትግል የሚቀብር
ገንጣይ ተገንጣይ፤ ሀገር አቃጣይ
መተራመስ፤ ሀገር የማስቀረስ “ሲሳይ”
ታይቶህ ኖሯል እንደ ራእይ?
ጥግህን የያዝከው፤ በሩቁ ያረፍከው?
ቀድመህ የወደከው?፡

**ጥላሁን፦** ዘረኛ ሙሰኛ፤ የቀን ጅብ ቀማኛ
ዝርፊያ ያልጠገበ ሀገርን የጋጠ፤
ባንዲራ የረገጠ
ታሪክ ያለ ተረት፤ ድጋይ ያለ ሐውልት፤
የሰደበ መስሎት
ሀገር ያረከሰ፤ ትውልድ ያስለቀሰ
እንኳንስ አላየህ አገዛዝ ዘረኛ
የቀረብህ ቢኖር የትግል ወሬኛ
የዘመን ቀበኛ።

**ጥላሁን፦** የጮኽላት ሀገር፣ ያዜምክለት ሕዝብ
ጨለማው ተገፎ፡ ደመናው ሲዘንብ
ዳግም ሲውለበለብ፡ ባንዲራችን በሀገር
አንድነቷን ጠብቃ፡ በኢትዮጵያዊነት ድምበር
ኢትዮጵያዊነት አብቦ፡ ሕዝባዊነት ሲደመር
ያኔ ተገላበጥ ታሪክ ለመሥራት
ዛሬ ግን ይቅርብህ ተኛ ተከራመት
ህያው ታሪክህን እንደጠበካት!፡

የጥላሁን ግዛው 50ኛ ዝክረ ሙት ዓመት አስመልክቶ የተገጠመ
ታህሳስ 19 ቀን 2012 ዓ.ም. (December 29, 2019)

ያ ትውልድ ተቋም (703) 300 4302
yatewlid@gmail.com
http://www.yatewlid.com,
http://www.yatewlid.org

<<ያ ትውልድ ተቋም>> የዛሬ ሰባት ዓመት የጥላሁን ግዛውን 43ኛ ሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ ያዘጋጀነውን ለ50ኛ ዓመት መዘከርታው በማሻሻል የዘመኑ ተጋሪ ትውልድ ቁራጭ ሻማ በመለኮስ የኅሊና ጸሎት ያደርግለት፣ የአሁኑ ትውልድ ታሪኩን ያውቀውና ለትውልድ ይተላለፍ፣ ይዘከር ዘንድ አቅርበንላችኋል።

<<ያ ትውልድ ተቋም>> ለጥላሁን ግዛው ቤተሰቦች፣ ዘመድ ወዳጆች፣ ለዘመኑ ተጋሪ ትውልድ፣ ለአሁኑ ትውልድና ለመጪው ትውልድ ታሪክን በአግባቡ በመዘገብ የያ ትውልድ ፈርጦች ተረስተውና ተዘንግተው እንዳይቀሩ ያቅማችንን እያደረግን እንገኛለን። በዚህ የጥላሁን ግዛው 50ኛ ዓመት ዝክረ ሙት ዓመት  ሀዘናችሁ ሀዘናችን፣ ስሜታችሁ ስሜታችን፣ ቁጭታችሁ ቁጭታችን መሆኑን እንገልጻለን።

ልክ የዛሬ 50 ዓመት ታህሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም. ከታናሽ ወንድሙ መኮንን ሲሳይ ጋር በመሆን ከስድስት ኪሎ በስተጀርባ አፍንጮ በር በሚባለው አካባቢ ፍቅረኛውን ዮዲት ታዬን ለመሸኘት ታክሲ ሊያሳፍራት ወደ መኪና መንገድ ወጡ። ሰዓቱ በግምት ከምሽቱ አንድ ሰዓት ከሩብ ይሆናል። አንድ ታርጋ የሌላት መኪና ቀረብ በማለት የሞት ጥይቷን ጀግናው ወጣት ላይ አርከፈከፈች። በኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ መሪ ቦታ የነበረው ጥላሁን ግዛው በግፍ ተገደለ። ጥላሁንን በመግደል የፊውዳሉን ሥርዓት የግፍ አገዛዝ ዕድሜ ለማራዘም ያለሙት ግድያው ቢሳካላቸውም ትግሉን ሊገድሉት አልቻሉም።

በጥላሁን ደም የትግል መፈክሮች ተጻፉ፤ ልቦች ቆርጠው ተነሱ፤ “ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ?” ተዘመረ። “አትነሳም ወይ! አትነሳም ወይ! የግፍ አገዛዝ አይበቃህም ወይ” ጩኸቶች በርካታ ጥላሁኖችን ወለዱ። “ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ እንደሆችሚኒ እንደ ቼኩቬራ” የበርካታዎችን ልብ አሸፈተ። የጥላሁን ድምጽ ከመቃብር ጮኸ፤ “መሬት ለአራሹ” በጥላሁን አጥንት ተገነባ። ብሶትና ቁጭት ያንገበገበው ተማሪና ግፍና መከራ የሰለቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ የረዥም ጊዜ ትግል ውጤት አምጠ! አምጠ! ከጥላሁን ግዛው እልፈት አራት ዓመት በኋላ የካቲት 1966ን ሕዝባዊ አብዮት ወለደ።

ጥላሁን ግዛው ከአባቱ ከንቡረዕድ ግዛው አበራና ከእናቱ ከወ/ሮ ደሴ አዱዬ ረታ በ1933 ዓ.ም. በራያና ቆቦ፤ አጠርሻ በመባል እምትታወቀው የገጠር መንደር ይወለዳል። ጥላሁን ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ ዕድገቱን በአደረገባት በገጠሯ አጠርሻና ሰንደይ የቤተክህነት ትምህርቱን እስከ ዳዊት ይከታተላል። የመጀመሪያዎቹን ዓመታት ዕድገቱን ከሴት አያቱ ከወ/ሮ ጥሩ ለገሠ ጋር የነበረው ጥላሁን እናቱ ሌላ ትዳር ይይዙና ወደ ላስታ አውራጃ ጊዳኖ ወረዳ አንጎት ሲጓዙ አብሮ በመሄድ ዕድገቱን ያደርጋል። ጥላሁን ወደ ዘመናዊ ት/ቤት በመዛወር ወልዲያ ጣይቱ ብጡል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት  ጀመረ።

ቀጠን ብሎ ረዘም ያለው ቀይ ሸበላ ወጣት ጥላሁን በመጀመሪያዎቹ አሥራዎቹ ዕድሜው ላይ ከአባቱ ጋር ወደ አዲስ አበባ በመምጣት እንጦጦ ሚሽን አዳሪ ት/ቤት በመግባት የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ተከታተለ። ጥላሁን በማስከተልም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ኮተቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በከፍተኛ ውጤት በማጠናቀቅ በ1959 ዓ.ም. የቀድሞው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (ቀ.ኃ.ሥ) ዩንቨርስቲ የአሁኑ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ሊገባ ችሏል።

የልዕልት ሣራ ግዛው ወንድም ጥላሁን ግዛው ከባላባት ቤተሰብ ቢወለድም ዕድገቱ ከገበሬ ልጆች ጋር ነበር። በገጠር ኑሮው ከአካባቢው ሕዝብ ጋር ለመመሳሰል በአለባበሱም ሆነ በባህሪው ይጥራል። በተማሪነት ዘመኑም ጊዜውን የሚያሳልፈው ከመሰል ተማሪ ጓደኞቹ ጋር እንጂ ከባለስልጣንና ከከበርቴ ጋር አልነበረም።

የጥላሁን አንባቢነት ደግሞ የተለየ ነበር። ከቤተክህነት ት/ቤት የጀመረውን የማንበብ ባህል አዲስ አበባ እንጦጦ ሚሽን አዳሪ ት/ቤት ሲገባ ይበልጥ አጎለበተው። የጥላሁን የመማርና የማንበብ ልምድም

እየተገነዘበ ከአደገበት የገበሬ ጎስቋላ ሕይወት ጋር በማጣመር የኢትዮጵያን የፖለቲካ አቅጣጫ ለብዙኃኑ በሚስማማ መልክ ለመቀየር ገና በለጋ ዕድሜው ያውጠነጥን ያዘ። ጥላሁን በቀ.ኃ.ሥ. ዩንቨርስቲ የሶሻል ሳይንስ ተማሪ በመሆን ባገኘው ከፍተኛ ነጥብ መሠረት የመጀመሪያው ምርጫው ወደሆነው የፖለቲካ ሳይንስ የትምህርት ክፍል መግባት ይበልጥ የሀገሩንና የዓለምን ፖለቲካ በሚገባ በመረዳት ግንዛቤ እንዲያገኝ እረድቶታል።

በኢትዮጵያ የተማሪዎች ትግል ከ1956 ዓ.ም. ቀደም ሲል የተፈጠረው የግራ ኃይሎች አስኳል ተጠናክሮ «አዞዎች» የተሰኘ ስብስብን በመፍጠር 1957 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ተማሪዎች የትግል መርህ «መሬት ላራሹ» መሆኑ ይፋ ተደርጎ መጋቢት 4 ቀን 1957 ዓ.ም. «መሬት ላራሹን የምትሹ፤ ተዋጉለት አትሽሹ» እያሉ ተማሪዎች በአደባባይ ሰልፍ በወጡ ወቅት የ11ኛ ክፍል ተማሪው ጥላሁን በሰልፉ ተሳትፏል። በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ጉልህ ስፍራ የያዘው ይህ ቀን ተማሪዎች በኢትዮጵያ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ግንኙነት ትልቅ ሚና በሚጫወተው በመሬት ይዞታ ላይ ማተኮራቸው አዲስ የፖለቲካ ሥርዓትን ለማምጣት እንደሚታገሉ ያመላከተ ነበር። ለዚህም በኢትዮጵያ ላለው አጠቃላይ ችግር ተጠያቂው የጉልተኛው ሥርዓት መሆኑን አመልካች ነበር። በወቅቱ ሶሻሊዝም የኢትዮጵያን ችግር የሚፈታ ሥርዓት መሆኑም የበርካታዎችን ድጋፍ አገኘ። ተያይዞም የመጻፍና የመደራጀት መብት ጥያቄዎች ይነሱ ጀመር። የዚህም ትግል ውጤት ዝነኛውን የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ማህበር «ኡዙዋ» USUAA (University Students Union of Addis Ababa) በማስገኘት በኢትዮጵያ ተማሪዎች የፕሬስ ነጻነት ታሪክ ውስጥ ቀዳሚውን ሥፍራ የያዘውን «ታገል» በመባል የሚታወቀውን ልሣን አስገኘ።

ጥላሁን ግዛው የ«አዞዎቹ» ዓላማ አራማጅና በኋላም ለመሪነት ለመታጨት የበቃ ወጣት ነበር። በ1961 ዓ.ም. በተደረገው የ«ኡዙዋ» ፕሬዘዳንታዊ ምርጫ በመኮንን ቢሻው ቢሸነፍም በቀጣዩ ዓመት ኅዳር 1962 ዓ.ም. በተደረገው ፕሬዘዳንታዊ ምርጫ በከፍተኛ ድምጽ ብልጫ ሊያሸንፍ በቅቷል። ጥላሁን በፕሬዘዳንትነቱ ቀዳሚው ሥራው የተማሪውን የመናገር፣ የመጻፍና የመደራጀት ነጻነት ይበልጥ ማጠናከር ሆነ። ለሁለት ወር ብቻ በፕሬዘዳንትነት ሕይወቱ የኖረው ጥላሁን የተለያዩ ሀሳቦች እንዲንሸራሸሩ በማበረታታቱ የሚታወቅ ታጋይ ነበር። ያ ትውልድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወት መሻሻል ያለምንም ስስት ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠ በመሆኑ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ ነበር። ጥላሁን ግዛው ከባላባት ቤተሰቦች የተወለደ ቢሆንም መደቡን ለደሀው ገበሬ፣ ሕይወቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ክብሩን ለሰንደቅ ዓላማው የሰጠ የያ ትውልድ ብርቅዬ ወጣት ነበር። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል መሠረታዊ አቅጣጫ እንዲይዝና የመደራጀት አስፈላጊነትን የጠቆመ አርቆ አስተዋይ ነበር። ንጉሡ በሽንገላ፣ በምክር፣ በቤተሰባዊ ግንኙነት፣ በቁጥጥራቸው፥ በመዳፋቸው ሊያስገቡት ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም «እምቢኝ ለሕዝቤ» በማለት ስለ መብትና ነፃነት የተሟገተና በርካታዎችን በአምሳሉ የቀረጸ የዚያ ትውልድ ፍሬ ነበር። ጥላሁን በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ የጎላ ስፍራ እየያዘ መምጣት ንጉሡና ባላባቱ ጥርስ ውስጥ ገባ። ጥላሁንን በማስወገድ ለሌላው ተማሪ መቀጣጫ በማድረግ ትግሉን ለማለዘብ የንጉሡ ነጭ ለባሾችና የፀጥታ ሠራተኞች በሄደበት ቦታ ሁሉ በመከታተል ያጠኑት፥ ያስፈራሩት ጀመር።

ታላቁ ታጋይ ታህሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም. አለፈ፤ ጥላሁን ግዛው አረፈ። ከደግነቱ፣ ከታላቅ ተሰጥዎው፣ ከነጥልቅ እውቀቱ፣ ከነብሩኅ ልቡ፣ ከነውብ ተፈጥሮው፣ ከነጀግና ዓላማው፣ ከነሀገር ፍቅሩ...ተከተተ። ለመብት-ለነፃነት-ለእኩልነት-ለእውነት...እንደሰበከ፣ እንደቃተተ፣ እንደዋተተ...ተገደለ። ለገበሬው እንደጮኸ፣ ለሀገር እንደዘመረ፣ ኢትዮጵያዬ እንዳለ የዛሬ 50 ዓመት አመለጠ። ብሶትህ ብሶቴ ብሎ «መሬት ላራሹ» እንደፈከረ፣ ለአዲስ ሥርዓት እንደሰበከ በአጭር ተቀጨ።

ጥላሁን በጥይት ከተመታ በኋላ የሕክምና ዕርዳታ ይደረግለት ዘንድ በየካቲት 12 ሆስፒታል ቢወሰድም ከመሞት ሊያመልጥ አልቻለም። የጥላሁንን መመታት የሰሙ ተማሪዎች ሆስፒታሉን አጨናንቀውት «አድኑልን» ጩኸታቸውን ቢያሰሙም አልተሳካላቸውም። ጥላሁን ግዛው አርፏል።

ተማሪዎቹ የጥላሁንን አስከሬን ወደ ስድስት ኪሎ የዩንቨርስቲ ቅጥር ግቢ በመውሰድ ከመላው የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከመጡ ተማሪዎች ጋር የሃዘኑ ተካፋይ ሆነዋል። የጥላሁን ታሪክና የትግሉ ዓላማ በግጥምና በስድ ንባብ እየተሰማ የሐዘን መግለጫው ዝግጅት እየተካሄደ በቀጣይነት በተማሪዎች ሰልፍ ታጅቦ በክብርና በጀግንነት በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የቀብሩ ሥነ ስርዓት ይፈጸም ዘንድ የዩንቨርስቲው ተማሪዎች ያደረጉት ጥረትና ተጋድሎ በንጉሡ ጸጥታ ኃይሎች አስገዳጅነትና ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ ተጨማሪ ተማሪዎችን ሕይወት ቀጥፎ አስከሬኑን ከተማሪዎቹ በመወሰድ አርቆ ለመቅበር የተደረገው ትርዕይት ሊታወስ የሚገባው የአገዛዙን ጨካኝነት አመላካች ነበር።

የጥላሁን ግዛው አስከሬን ከተማሪዎቹ በኃይል እርምጃ ከተወሰደ በኋላ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ታህሳስ 22 ቀን 1962 ዓ.ም. በአካባቢው ተማሪዎች ሰልፍ አጃቢነትና መላው ዘመድ አዝማድ በተገኙበት በትግራይ ክፍለ ሀገር በማይጨው ሕዝባ ማርያም ተፈጸመ።

ጥላሁን ግዛው በትውልድ ቦታው አንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና አንድ መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በስሙ ተሰይመውለታል።

«ያ ትውልድ» ተቋም ከተነሳበት ዓላማ አንዱ የዚያን ትውልድ ሰማዕታት መዘከርና ታሪካቸውን ለትውልድ ማስተላለፍ በመሆኑ የጥላሁን ግዛውን 50ኛ የሙት ዓመት መዘክር ስናስታውስ በጥልቅ ሐዘን ነው። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል አንድ ሁነኛ መመኪያውን ያጣበት ቀን ታህሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም.። ያ ትውልድ ይዞ የተነሳው ለሀገሩ ልማትና ለሕዝቡ የመብት ጥያቄ ተጋድሎ በጥላሁን ግድያ ተንቦግቡጎ የካቲት 1966ን ሕዝባዊ ዓመጽ በመላው ሀገሪቷ በማስነሳት የፊውዳሉን ሥርዓት ገርስሦ ጥሎታል። ኢትዮጵያ ሀገራችን አንድነቷን ጠብቃ የልጆቿ መብት የተከበረባትና ለሀገር ብልጽግናና ለልማት የተከፈለው የያ ትውልድ ሰማዕታት ደም ከንቱ እንደማይቀርና ሁሌም በትውልድ ሲዘከር፣ ሲታወስ እንደሚኖርና የትግላቸውም ፍሬ ኢትዮጵያ ሀገራችንንና ልጆቿን ከፍ ከፍ እንደሚያደርጋት እምነታችን የጸና ነው።

የዛሬ 50 ዓመት በኢትዮጵያ የነበረው የጭሰኛና የባላባት ሥርዓት ያከትም ዘንድ "መሬት ለአራሹ" ከታጋዩ አንጻር መሪ መፈክር ሲሆን ከአገዛዙ አንጻር ደግሞ አስከፊ መፈክር ነበርና ጥይት አስመዝዟል። የ "መሬት ለአራሹ" ጥያቄ የሥርዓት ለውጥን ይጠይቃልና። የ "መሬት ለአራሹ" መፈክር የባላባታዊ ሥርዓትን ማክተም ይፈልጋልና። ለሀገርና ለሕዝብ በሚደረጉ ትግሎች ሁሌም መስዋዕትነትን የሚከፍሉ ግምባር ቀደም ፋና ወጊዎች ይኖራሉ፤ አሉም። ጥላሁን ግዛው ከነዚህ የሚመደብ በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ከፍተኛ ክብር የሚሠጠው ጀግና ነው። ዛሬ ጥላሁን ግዛው ከመቃብር በላይ ስሙ ይታወሳል፤ ወደፊትም። በትግል መሞት ሕይወት ይህ ነው!

የያ ትውልድ ታሪክ ሕያው ነው!!!
«ያ ትውልድ ተቋም» ለመረጃ ምንጭነት!
የተጐዱ ወገኖችን ለመርዳት!
ለያ ትውልድ መታሰቢያነት!

**«ያ ትውልድ ተቋም»**

- ስልክ ፡ (703) 300 4302
- ኢሜል : yatewlid@gmail.com,
- ድረ ገጽ : http://www.yatewlid.com, http://www.yatewlid.org, www.redterror.org, www.thatgeneration.org
- ምስለ ገጽ : yatewlid

ታህሳስ 19 ቀን 2012 ዓ.ም. (December 29, 2019)
ዋቢ ጽሁፎች

- «ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ» ቅጽ አራት ሜጋ አሳታሚ 1991 ዓ.ም. አዲስ አበባ
- «ያ ትውልድ» ክፍሉ ታደሰ፤ ቅጽ አንድ ኢንዲፔንደንት አሳታሚዎች ሰሜን አሜሪካ
- <<ያ ትውልድ ተቋም>> መጣጥፎች

